

# ሰንደቅ ዓላማችን

ከጠቢያ ድላይ

የኢትዮጵያውያን መለያ
የዜግነት መኩሪያ
የፓን አፍሪካኒዝም ዓርማ
የነፃነት አውድማ
የኤክሶዶስ ምሣሌ
የራስታዎች ኦርጅናሌ
ውብ ማራኪ ታሪካዊት
ህብረ ቀለም ኢትዮጵያዊት
ተስፋ ልምላሜና ሃብታችን
ሃይማኖት አበባና ፍሬያችን
የመሥዋዐትነትና የጀግንነት ውጤታችን
ተውለብለቢ ለዘላለም በቀያችን
በእናት ምድር በኢትዮጵያችን
ነሽና የአንድነት መግለጫችን
የዜጎችሽ የሁሌ አርማ
የኛዋ ሰንደቅ ዓላም
ከፍ ብለሽ ተውለብለቢ
በኛው ቀዬ በኛው ግቢ።

